ታህሳስ 2017
ቅፅ ፩ | ቁጥር ፩

# ንስንስ

## ቋንቋ እና ማንነት

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ
በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ
የምትታተም መጽሔት

QUEERETHIOPIA
ኩዊር ኢትዮጵያ

etqueerfamily@gmail.com
ethioqueer
queerethiopia.com
t.me/queeret
QueerEthiopia

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሿዋል ወይም ኤሴክሿዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ’ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።

# ማ
# ው
# ጫ


1 ቋንቋ በ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ

2 አፈ ታሪኮች እና አለመግባባቶች

3 ቀልድ እና ማንነት

4 ሙዚቃ

5 ኢሞጂ ቢሆኑ...

# የአርታዒያን መልዕክት

ኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 በላይ ቋንቋዎች በአንደበታችን ላይ ይደንሳሉ። አንዳንዶቹም የራሳቸው ፊደል ኖሯቸው በትውልዶች እንደተሸመኑ ደመቅ ያሉ ጥልፎች ያገለግላሉ። ጥንታዊው የግእዝ ቋንቋ የበለጸጉት ቅርሶቻችን ማስረጃ ቢሆንም በዚህ የቋንቋ ውድ ሀብት ውስጥ የኩዊር ማንነቶችን የሚገነቡ ቃላት አይገኙም። ቋንቋ ትግላችንን ፣ ደስታችንን እና ታሪካችንን የሚያንፀባርቅ መስታወት ነው፤ ነገር ግን ለብዙዎቻችን በLGBTQ+ ማህበረሰብ ውስጥ ላለነው ሰዎች አያገለግለንም። የዉጭ ሰዎች እንደሆንን ምልክት የሚያድርጉብንን መለያ መጠሪያዎች እየሰማን እናድጋለን። እንደ “ግብረሰዶም” (ማለትም “የሰዶም ስራ”) አይነት ቃላቶችን በየቤቶቻችን፣ ትምህርት ቤቶች እና በሄድንበት ቦታ ሁሉ ሲያስተጋቡ እንሰማቸዋለን። ይህ ወደ የሚያሰቃይ ጸጥታ ይመራናል።

አብዛኛውን ጊዜ መኖራችንን በሚክድ ማህበረሰብ ውስጥ የምንመርጣቸው ወይም የተመረጡልን ቃላቶች ስለራሳችን ያለንን ግንዛቤ አብሶም ለእራሳችን ያለንን አቀባበል ይቀርፃሉ። እንደ “ጌይ” ወይም “ሌዝቢያን” ያሉ የእንግሊዘኛ ቃላቶች መጠለያ ቢሆኑንም የባዕድ አገር ቃላቶች እንደሆኑ ስለሚሰማን ከኢትዮጵያዊነታችን ያፋቱናል። ይህ ትግል በሁለት ዓለማት መካከል እንድንተሳሰር እና ሁሉንም የማንነቶችን ያማከለ ቋንቋ እንድንፈልግ ያደርገናል።

ቋንቋ ኃይል አለው፤ ሊያነሳ ወይም ሊቀብር፣ ሊያገናኝ ወይም ሊያገል ይችላል። ማንነታችንን ስንመረምር፣ መመርመርን እንጋብዛለን፤ የወደዱትን የፊልም ርዕስ በመጠቀም ማንነትዎን እንዴት ይገልጹታል? መንፈስዎን የሚይዙት ሶስት ኢሞጂዎች የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ቀለል ያሉ ጥያቄዎች ከእውነቶቻችን እና ከትክክለኛ ማንነታችን ጋር እንድንገናኝ አስችለው ወደ ፈጠራ ይመሩናል።

ይህ 14ኛው የንስንስ እትም የተግባር ጥሪ ነው፤ ታሪኮቻችንን እና ልምዶቻችንን የሚያከብር እንዲሁም የሚያበረታታን እና እንድንቀጥል የሚያስችለን ቋንቋ መፍጠር እንፈልጋለን። ኲዊርነታችንን ለማክበር አዳዲስ ቃላትን በጋራ ማዘጋጀት እንደምንችል ተስፋ እናደርጋለን።

# ቋንቋ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ

ኢትዮጵያን ሀገሬ ብለን ለምንጠራ ወይም ጠርተን ለምናቅ ሰዎች ስለራሳችን ማወቅ ብዙ ግዜ የሚጀምረው ግብርሰዶም ከሚለው የግእዝ ቃል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም “የሰዶም ሥራ” ማለት ነው።




ይህ ቃል በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የሰዶምና የገሞራ ታሪክ የመነጨ ሲሆን እግዚአብሔር አምላክ በኃጢአተኞች ላይ ዲን እና እሳትን አዘነበ፣ ሁለቱንም ከተሞችና በእነርሱ ውስጥ ያሉትን ሁሉ አጠፋ። የሎጥ ሚስት እንኳን ወደ ኋላ ለማየት በመደፈሯ አልተረፈችም።

ቃሉ እንደ ከባድ ማስጠንቀቂያ ወይም እንደ “የጨዋ” ማሳሰቢያ ሆኖ ያገለግላል፤ እኛም ደግሞ ከሰዶም ጋር ከተመሳሰልን ወደ ምሳሌያዊ ጨውነት ልንለወጥ እንችላለን መመሳሰሉ የእውነት ይሁንም አይሁን። ይህ ችላ ለማለት የሚከብድ ትምህርት ነው።

# ቋንቋ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ



ከራሳችን ጋር ያለውን ግንኙነት ጨምሮ ሌሎች ግንዛቤዎችን ለመቅረጽ ቋንቋ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ብዙ ኩዊር ሰዎች ራሳችንን ለመቀበል እንቸገራለን ምክንያቱም ሁልጊዜ እንደ ኃጢአተኞች የሚፈርጅ ቋንቋ እየሰማን ስለምናድግ ነው። አሉታዊ ማዕቀፉ በጣም የተስፋፋ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከሱ ማምለጥ ሲያቅተን ይስተዋላል። ማንነታችንን ለመግለፅ ያለው ብቸኛ የሀገር ውስጥ ቃል “ግብረሰዶም” ነው።

ከራሳችን ጋር ያለውን ግንኙነት ጨምሮ ሌሎች ግንዛቤዎችን ለመቅረጽ ቋንቋ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ብዙ ኩዊር ሰዎች ራሳችንን ለመቀበል እንቸገራለን ምክንያቱም ሁልጊዜ እንደ ኃጢአተኞች የሚፈርጅ ቋንቋ እየሰማን ስለምናድግ ነው። አሉታዊ ማዕቀፉ በጣም የተስፋፋ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከሱ ማምለጥ ሲያቅተን ይስተዋላል። ማንነታችንን ለመግለፅ ያለው ብቸኛ የሀገር ውስጥ ቃል “ግብረሰዶም” ነው።

# ቋንቋ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ

“ግብረሰዶም” ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመገለል ስሜት ለማስወገድ አብዛኞቻችን እራስን መቀበልን እና በራስ የመተማመን ስሜትን የሚያመለክቱትን የእንግሊዝኛ ቃላትን እንጠቀማለን። እንደ “ጌይ” ፣ “ሌዝቢያን” እና “ኩዊር” አይነት ቃላቶች እዚህ ውስጥ ይካተታሉ። እነዚህ እና ሌሎች መሰል ቃላቶች የአዎንታዊነት ስሜት ቢፈጥሩብንም ተመልሰው ግን የኩዊር ማንነታችንን ከኢትዮጵያዊ ማንነታችን ጋር በመለያየት የውጬኝነት ስሜት እንዲፈጠርብን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ቃላቶች ትክክልኛ ማንነታችንን መግለፅ ስለማይችሉ የውስጣችን አለመጣጣምን ያባብሱታል።



# ቋንቋ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ

ኢትዮጵያዊነታችንን በኲዊርነታችን ጋር የምናግባባትን
መንገድ ስንፈልግ እንደክማለን። ቋንቋ ይህን ሁሉ የሚቀርጽ
አንድ መንገድ ነው። በአገራችን የበለጸጉ ቋንቋዎች ውስጥ
አልተሰየምንም፤ ይህም ህብረተሰቡ ኃጢአተኞች እንደሆንን
ወይም የምዕራባውያን አስተሳሰቦች ተጽዕኖ ነው ብሎ
እንዲያስብ ቀላል ያደርገዋል።

-ብስራት



# ቋንቋ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ

በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ ቋንቋ ከመግባቢያ ቁልፍ በላይ ሊሆን ይችላል። ሰዎች በሚነጋገሩበት ቋንቋዎች ላይ የተመሰረቱ አመለካከቶች አሉ።

እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለምሳሌ እንግሊዝኛን በብዛት የምትናገሪ ከሆነ እና የ**LGBTQ+** ማህበረሰብ አካል ከሆንሽ ሰዎች የኩዊር ማንነትሽ የምዕራባውያንን ባህል እየተከተልሽ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ።

ቋንቋ ራሱ የራሱ የሆነ መለያ አለው እና ሰዎች እንቺ በምትናገሪው ቋንቋ ላይ በመመስረት ማንነትሽን ሊያዋርዱ ወይም ሊንቁ ይችላሉ። በኛ ማህበረሰብ ውስጥ ዴቲንግ ላይ እንኳን እነዚህ አመለካከቶች አሉ።



# አፈ ታሪኮች እና አለመግባባቶች

”

ከትንሽ ጊዜ በፊት ኩዊር መሆኔን ከነገርኳት ልጅ ጋር እየተጨዋወትን ነበር። አሁንም ገና ሃሳቡን ለመቀበል እየተንገዳገደች ቢሆንም የሚያልፍ ነገር እንዳልሆነ ታውቃለች። ለማንኛውም እያወራን እያለ ቀለል አድርጋ “እስካሁን ቦይፍሬንድ አልያዝሽም አይደል? ስለ ጋብቻ እና ልጅ ስለመውለድ ብታስቢበት ይሻልሻል...” አለችኝ። ከሷ መምጣቱ በጣም ግራ ያጋባል። ከዚህ የተሻለ ምላሽ ስላልነበረኝ “ደስተኛ የሆንኩበት የፍቅር ግንኙነት እንዳለኝ ታውቂያለሽ? ባይገርምሽ ቦይፍሬንድየው እኔው ነኝ!” አልኳት። የነገሮች መቀያየር! ምላሹ ነገሮችን የባሰ... አጨናናቂ ቢያደርጋቸውም አስፈላጊ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንድ ሰዎች አይረዱትም ግን ያው እዚሁ ለመቆየት እና ምርጡ ህይወቴን ለመኖር ነው የመጣሁት!

# አፈ ታሪኮች እና አለመግባባቶች

እንደ ሌዝቢያን ለምታውቀኝ አንድ ሌዝቢያን ጓደኛዬ አሁን ከአንድ ወንድ ጋር ዴት እያደረኩ እንደሆነ ነገርኳት። መጀመሪያ ቀልዴን ነበር የመሰላት። እና በጣም ገራሚ የማብራሪያ ሂደት ነበር። ምክንያቱም እሷም ማንነቷን እንድትገነዘብ ረድቷታል። እሷም ሌዝቢያን እንደሆነች ነበር የምታስበው። ከዛ ብዙ ሰዎች ስለዚህ ነገር ያናግሩኝ ጀመር። “ደግሜ ባይ ሆንኩኝ” ወይም “አሁን ሌዝቢያን ነኝ” ይላሉ። እኔም መስመሩን አሳያቸዋለሁ። እንደዚህ አይነት ብዙ ንግግሮች ነበሩን።

# ቀልድ እና ማንነት

አንዳንድ ሰዎች ስለ ጉዳዩ የሚናገሩበት መንገድ ምን ያህል ሞኝ እና ምክንያታዊ እንዳልሆነ ለማሳየት በእርግጠኝነት ቀልድ እና ስላቅ በበለጠ መንገድ እጠቀማለሁ።

— ብርሀን



# ቀልድ እና ማንነት

እኔ እንደማስበው ከኩዊር ጓደኞች እና "ቀጥ" ጓደኞች ጋር በተለየ መንገድ እጠቀመዋለሁ። ከ"ቀጥ" ጓደኞቼ ጋር እምብዛም አይመቸኝም ምክንያቱም አፍ እላፊ የሆኑ ነገሮች እንዲናገሩ ማለፊያ የሚሰጣቸው ስለሚመስለኝ ነው። ከኩዊር ጓደኞቼ ጋር የበለጠ ክፍት ነው። ወደ ማንነት ሲመጣ ከባባድ ሃሳቦችን ሳልቀልድ መናገር ይከብደኛል። ማለት ኮስተር ብዬ “ይህ ነገር እና ያ ነገር ይሰማኛል” ብዬ ማውራት አልችልም። “ሃሃ ግራ የመጋባት ዘመኔ ላይ ነኝ” ብዬ ቀልዳለሁ እንጂ።

– ሳራ

# የፍቅር ሕይወትዎ ጭብጥ ዘፈን ቢኖረው




የፍቅር ሕይወትዎ ማጀቢያ ዘፈን ቢኖረው
"ህይወቴ ማጀቢያ ዘፈን ቢኖረው
በርግጠኝነት ቴክ ሚ ቱ ቸርች
በሆዚየር ይሆን ነበር።" – ሲ.

ሙዚቃ

# ማይክል ቦልተን

## ሊን ኦን ሚ

– ናን





ብሌስ ዘ ቴሌፎን በለቢ ስፍሪ
ምክንያቱም የረጅም ርቀት
ግንኙነት ውስጥ ስለሆንኩኝ ብዙ
ንግግራችን የሚወሰነው
በስልክ ስለሆነ ነው።" – ሳራ



# ኢሞጂ ቢሆኑ...



በህይወቴ ውስጥ ቀለል ያለ ፣ የሙከራ ፣ ተጫዋች እና ክፍት በሆንኩበት ቦታ ላይ ነኝ። እናም ምስጢራዊ ዓይነት።



ወደ ነጻነቴ ለመመለስ እየሞከርኩ ነው። ውሃ የሰላም ስሜት ይሰጠኛል። ወደ ሰላማዊ ቦታ ለመድረስ እየሞከርኩ ነው።



በህይወቴ ውስጥ በጣም ወሳኝ ቦታ ላይ እንዳለሁ ይሰማኛል። ስለዚህ ይህ የእኔ ማንነት በብዙ ግራ መጋባት የተደገመ ነው እና ምናልባት ያንን ለማወቅ ጊዜው አሁን ነው ፣ ግን የት እንዳለሁ አላውቅም። የሆነ ቦታ እንደምሄድ አውቃለሁ እና ግራ መጋባቱ የመጣው በዚሁ ነው።

# ኢሞጂ ቢሆኑ...



# ኢሞጂ ቢሆኑ...



ምክንያቱም ማንነቴ አፍቃሪ እና ተጫዋች ነው።
አፍቃሪ እና ተጫዋች ብቻ ሳይሆን አሰደሳች፣ እንግዳ ተቀባይ እና ትልቅ ጉልበት ያለው ጎን አለው።
ክፍት አእምሮ እና ለአዳዲስ ነገሮች የማወቅ ጉጉት

# ኢሞጂ ቢሆኑ...



የመጀመሪያው ስለ ድንቅ ሴቶች ነው።
ሁለተኛው? እንግዲ እኔ አድናቂ ብቻ ሳልሆን በእርግጠኝነት ለነሱ "መስህብ" እንዳለኝ እንዲታወቅ ትንሽ ፍንጭ ነው።
ሦስተኛው ኢሞጂ ደግሞ የሴት አፍቃሪ ሴት ማንነቴ ግሩም ብቻ ሳይሆን “ጣሊያን ግሩም!” መሆኑን የማሳይበት መንገድ ነው። ልክ እንደ ሚጣፍጥ ፓስታ፤ ትንሽ የሚያቃጥል፣ የሚጣፍጥ እና በዛ ባለ ስጎ የተሰራ ፓስታ!

# ኢሞጂ ቢሆኑ...



በመጀመሪያ እና ከሁሉም በላይ ግራ የተጋባ ኢሞጂን እመርጣለሁ።
አናናስ፤ ደስ የሚል መልክ ያለው ፍራፍሬ እንደሆነ ስለተሰማኝ እና ተመሳሳይ ስሜት አለው ብዬ ስለማስብ ነው።
ልብ፣ የአናቶሚካል ልብ ምክንያቱም አስፈላጊው ነገር እንደሆነ ስለሚሰማኝ፣ ስለሱ ብዙ ማሰብ ወይም ምሁራዊ ማድረግ አልወድም። ግራ የገባኝ ግራ ስለገባኝ ነው።

| የተወረሰ | በእኛ የተፈጠረ |
|---|---|
| TWINK (ትዊንክ) | ሴት ወዳጅ |
| GIBRESODOM (ግብረሰዶም) | ጂዎች |
| FAGGOT (ፋጌት) | ወንዳዊ |
| | ሁለፍቅር |
| | ፋጤ |
| | ሴታዊ |

”

ቡሽቲ የሚለውን ቃል በጣም ነው የምጠላው ሰዎች ሌሎችን ለማሸማቀቅ ስለሚጠቀሙበት ነው፤ ያቅለሸልሸኛል።

– ለም

# ኀስኀስ

ቋንቋ እና ማንነት